**KINIJIT SUPPORT ASSOCIATION - AMERICA**
**በአሜሪካ የቅንጅት/መኢአድ የድጋፍ ሰጪ ማሕበር**
**1629 K Street, NW, Suite 300 ▪ Washington, DC 20006**
**Tel: (202) 973 - 0170 ▪ Fax: (202) 331-3759**
**web: www.ksa-america.org**

**ማርች 21 ቀን 2010 ዓ. ም**

# በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት / መኢአድ ድጋፍ ሰጪ ማህበር 9ኛ መደበኛ አጠቃላይ ጉባኤ ተካሔደ

በሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጪ ማህበር 9ኛ አጠቃላይ ጉባኤ ከ14 የአሜሪካን ግዛቶች በተውጣጡ የቻፕተር መሪዎችና ተወካዮች በኔቫዳ እስቴት፣ በላስቬገስ ከተማ፣ በቮልደር ስቴሽን ሆቴል ማርች 20 ና 21 ቀኖች 2010 ዓ. ም. በተቃናና በተሳካ ሁኔታ ተከናውኖአል።

በአካል ለመገኘት ያልቻሉ የሁለት ቻፕተር ተወካዮች በቴሌ ኮንፍራንስ በሁለቱም ቀናት ጉባኤ ሙሉ ተሳታፊ ሆነዋል።

የማኅበሩ ሊቀመንበር አቶ ግዛው ተሰፋዬ ባለፉት ሁለት አመታት ማህበሩ ያከናወነውን ዘገባ አቅርበው መልካሙን በማጎልመት ከስህተቶቻችን በመማር ለወገኖቻችን ጠንካራ አለኝታ እንድንሆን አስገንዝበው በሥራ ዘመናቸው ሥራቸውን ለማሳካት በሚጣደፉበት ወቅት ያሳዘኑት ካለ ይቅርታ በመጠየቅ የሚቀጥለውን የሥራ ዘመን በመሪንት ለሚረከቡት መልካም የሥራ ዘመን በመመኘትና በተፈለጉበት ሁሉ ለመርዳት ፈቃደኛነታቸውን ገልጸዋል።

ከዛም በማስከተል አቶ ስለሺ ጥላሁን እና አቶ ፀሀይ ደመቀ የኦዲትና ኢንስፔክሽንን በማስመልከት፣ እንዲሁም ፕሮፌሰር ሃብተጊዮርጊስ ቸርነት እና እቶ ኪዳኔ ምስክር የስነምግባር ኮሚቴን የሁለት ዓመት የሥራ ሪፖርት ለጉባኤው ተሳታፊዎች አቅርበዋል።

ጉባኤው በመርሃ ግብሩ እንዳሰፈረው በቅደም ተከተል በቀረቡት የሥራ ዘገባዎች ላይ በተለያዩ አርእስቶች በፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ስነስርአት ተወያይቶአል። መተዳደሪያ ደንቡንም በተመለከተ ተወያይቶ ደንቡን በማሻሻያ አንቀጾቹ መሰረት የማስተካከያና የማሻሻይ ሃሳቦች ካሉ እስከ ሜይ 21 ቀን 2010 ዓ. ም ከአባላት ለሥራ አመራሩ እንዲቀርቡ ተስማምቶአል።

ከጉባኤው ታዳሚዎች አንዱና እንጋፋው መምህር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በአላማ ስለመጽናትና ተቻችሎ መሥርት ሊያስገኝ ስለሚችለው ጥቅምና ሊገጥመው ስለሚችለው መሰናክል ምክር አዘል ትምህርት ሰጥተዋል።

ለቀጣዩ ሁለት ዓምታት ማኅበሩን የሚመሩ የሥራ አስኪያያጆችና በተለያዩ ኮሚቴዎች በሀላፊነት የሚያገለግሉ አባላትን ጉባኤው መርጦአል።

አዲሶቹም ተመራጮች ማኅበራቸውን በታማኝነት፣ በቅንነትና በትጋት የሚያገለግሉ መሆናቸውን በጉባኤው ፊት ቃለ መሃላ ፈጽመዋል።

እንደዚሁም ከአዲስ አበባ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላት የእንክዋን ደስ አላችሁና የፓርቲውን ወቅታዊ እንቅስቃሴ በማስመልከት ለጉባኤው በየተራ ንግግር አድርገዋል።

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ስለሰላማዊ ትግል ጥናታዊ ትምኅርት ቀረቦ ውይይት ተደርጎአል። በመጨረሻም የጉባኤው መልእክትና የአቋም መግለጫ ለአባላቱ ከተነበበ በህዋላ ስብሰባው ተጠናቆአል።

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት / መኢአድ የድጋፍ ሰጭና የልማት ማህበር